# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

21



የካቲት ፳፯—፲፱፻፷፱ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንና የኢትዮጵያ ሴቶች

የካቲት ፳፱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶች ቀን ሆኖ ሲታወስ ቆይቷል ። ይህ ቀን በዓለም ውስጥ ያሉ ጭቁን ሴቶች የትግል አንድነታቸውን የሚያሳዩበት ቀን እንዲሆን ያሳሰበችው ክላራ ዜትኪን ነበረች ። ዜትኪን ከታወቁት ታላላቅ አብዮታውያን አንዷ ስትሆን ለዓለም የኮሙኒስት እንቅስቃሴ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክታለች ። ለሴቶች መብትና ነፃነት በሚደረገው ትግል ውስጥ በግንባር ቀደምትነት በመሠለፍ በጀርመንና በዓለም አቀፍ ደረጃም በሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያበረከተችው ድርሻ ፍጹም የሚዘነጋ አይደለም ። በጀርመን ውስጥ የኮሙኒስት ፓርቲ ለመ መሥረት በተካሔደው ትግል ውስጥም ታላቅ ሚና ተጫውታለች ።

በ፲፱፻፲ ዓ. ም. በኮፐን ሀገን ውስጥ በተደረገው የሶሻሊስት ሴቶች ስብሰባ ላይ ክላራ ዜትኪን ይኸ ቀን የዓለም ጭቁን ሴቶች የሚያስታውሱት የትግል ቀን እንዲሆን ባሳሰበችው መሠረት እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ ሲከበር ቆይቷል ። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሴቶች ይህንን ቀን ያወቁት በቅርብ ጊዜ ቢሆንም ፤ ላለፉት ፳፯ ዓመታት በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገኙ ሴቶች በተለያየ እኳኋን አስታውሰውታል ።

የኢትዮጵያ ሴቶች ይህንን ቀን ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ ለማክበር መቻላቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ለረጅም ጊዜያት በጭቆና ቀንበር ሥር አውለው ያቆያቸውን ሦስቱን ጥምር ጠላቶች ለመደምሰስ ባደረጉት እንቅስቃሴ ከተቀዳጅዋቸው ድሎች አንዱ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል ። ይኸ ቀን ዛሬ የኢትዮጵያ ሴቶች ባገኙዋቸው አንዳንድ ድሎች ረክተው የሚቀመጡበት አይደለም ። ፍጹም አይደለም ። ገና ለሚቀራቸው ረጅም ጉዞ ወገባቸውን የሚያጠብቁበት ፤ የነሱ ነፃነት ከበዝባዥ ሥርዓት ጋር ያለውን ጥብቅ ግንኙነት በመረዳት ከመደብ ወንድሞቻቸው ጐን ተሠልፈው የሚታገሉበትና በትግል ላይ ከሚገኙ ሌሎች ሴቶች ጋር ክንዳቸውን የሚያስተባብሩበት ነው ።

የሴቶች ጥያቄ ከመደብ ትግል ተነጥሎ የማይታይ ከመሆኑም በላይ ፤ የሴቶች ነፃነት የሚረጋገጠው በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለው የመደቦች ቅራኔ መፍትሔ ሲያገኝ ነው ። ስለዚህም የዓለም ጭቁን ሴቶች ይኸንን ቃን ሲያከብሩ ፤ የዓለም አቀፍ አድኃሪ ኃይላትን ለመደምሰስ በሚደረገው ትግል ውስጥ ተገቢ ሥፍራቸውን መያዝ እንዳለባቸው ያስታውሳሉ ። ለፍትሕ ፤ ለነፃነት ፤ ለዲሞክራሲ በመቆም ለዚህ ዕንቅፋት የሆኑትን ያወግዛሉ ። ይቃወማሉ ። ይታገላሉም ።

ኢምፔሪያሊዝም የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ቀንደኛ ጠላት ነው ። ስለዚህም ለጭቁን ሴቶችም ይኸው ኢምፔሪያሊዝም ጠላት መሆኑ የታወቀ ነው ። የዓለም ጭቁን ሴቶች ይኸንን ቀን ሲያከብሩ በተለያዩ መንገዶች ለዚህ ለሕዝቦች ጠላት ያላቸውን ተቃውሞ ያሳያሉ ። በዚህም የትግል አንድነታቸውን ይመሠርታሉ ማለት ነው ።

በዓለም ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች በተለያዩ የእድገት ደረጃዎች ውስጥ እንደመገኘታቸው ይኸንን በዓለም የሚያስታውሱበት ሁኔታም ይለያያል ። በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ይኸ ቀን አድኃሪ ሥርዓት ከአንድ አገር ሲደመሰስ አርፎ እንደማይቀመጥ በማወቅ እንዳያንሠራራ የሚከላከሉበት ለነፃነታቸው ትግል ለሚያደርጉ ሌሎች ሴቶች ድጋፋቸውን የሚሰጡበትና መደቦችና የሰው በሰው መበዝበዝ እስከ መጨረሻው የሚጠፉበትን የኮሙኒስት ኅብረተሰብ ለመገንባት ትግላቸውን የሚቀጥሉበት ነው ። ይኸ ቀን በሶሻሊስት አገሮች በታላቅ ድምቀት ከመከበሩም በላይ ፤ እነዚህ ሴቶች ገና ድል ላላገኙ ፤ ነፃነታቸውን ላልተቀዳጁ ሴቶች ምሳሌነታቸውን የሚያሳዩበትም ቀን ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ በዝባዥ ሥርዓት ገና ባልተወገደበት በዚሁ ምክንያት ሴቶች በድርብ የሚጨቆኑበት ቦታዎች ያሉ ሴቶች ይኸ ቀን ከጭቆና ለመላቀቅ ትግል የሚያደርጉበት ፤ በበዝባ

ጉዞች ላይ ክንዳቸውን የሚያነሱበት ቀን ነው ። ይኸም ብቻ ሳይሆን ይኸ ቀን ያለፈው ትግላቸውን ድካምና ጥንካሬ የሚያስላስሉበት ፤ ድካማቸውን አስወግደው ወደፊት የሚጓዙበት ቀን ነው። ስለዚህም ይኸ ቀን በየቦታው ያሉ ጭቁን ሴቶች የትግል አንድነታቸውን የሚያረጋግጡበት ቀን ይሆናል ማለት ነው ።

የኢትዮጵያ ሴቶችስ ይኸንን ቀን እንዴት ነው የሚያከብሩት ?

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለዘመናት የተጫኑዋቸውን ሦስት ጠላቶቻቸውን ለመደምሰስ ያደረጉት ታላቅ ተጋድሎ ፍሬ ማሳየቱ ይኸንን በዓል በሌሎች ጭቁን እኅቶቻቸው ጐን ተሠልፈው ለማክበር እንዳስቻላቸው ቀደም ብሎ ተጠቅሷል ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ጭቁን ሴቶች ይኸንን የትግል ውጤት የሆነውን በዓል ለሌሎች ትግሎች መንገድ ጠራጊ መሆኑን ተገንዝበው በታላቅ ድምቀት ያከብሩታል ። ከጥምር ጠላቶቻቸው ጋር የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚያካሒዱትን ትግል የኢትዮጵያ ሴቶች እጃቸውን አጣምረው አይመለከቱም ። የሴቶች ድርብ ጭቆና የሰው በሰው መበዝበዝ ከተጀመረበት ወቅት የተነሣ በማንኛወም ገዢና ተገዢ መደቦች ባሉበት ኅብረተሰብ ውስጥ ያለ ነው ። ይኸም እንግዲህ ሴቶች ለነፃነታቸው የሚያደርጉት ትግል ከበዝባዥ ሥርዓት ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ያሳያል ። ከዚህ ተነሥተን ሴቶች ነፃ እንዲወጡ በመጀመሪያ ደረጃ በዝባዥ ሥርዓት መዋጋት እንዳለባቸው እንረዳለን ማለት ነው ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ጭቁን ሴቶች ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ጐን በመሠለፍ ከፊውዳሊዝም ፤ ከኢምፔሪያሊዝምና ከቢሮክራሲ ካፒታሊዝም ጋር ትግል ያደርጋሉ ። እነዚህን ጠላቶች በመደምሰስ ማለትም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ በማለፍ የሰው በሰው መበዝበዝ ወደሚያስወግድበት ወደሶሺያሊዝም ይሸጋገራሉ ። በዚህም ነፃነታቸውን ይቀዳጃሉ ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ሴቶች ይኸንን ዓለም አቀፋዊ በዓል የትግል ቀን አድርገውት ይውላሉ ማለት ነው ። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሴቶችም ጭምር ጠላቶቻቸውን ለመጣል ከረጅም ጊዜያት ጀምሮ በመሥዋዕትነት የታገሉ ቢሆንም ቀደም ብለው የነበሩት ትግሎች በየቦታው የተበታተኑና የተቀነባበረ መልክ ያላቸው ስላልነበሩ ፊውዳሊዝምን ፤ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ለማስወገድ አላስቻሏቸውም ። ነገር ግን የተጠራቀሙት ትግሎች በየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. መፈንዳት እነዚህን ጠላቶች ለመደምሰስ ብዙ ሁኔታዎችን ፈጥሯል ። የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ከግቡ ለማድረስ የሚያበቁ አንዳንድ እርምጃዎችን አስከትሏል ። ነገር ግን አብዮት ረጅም ፤ መራራና የጭቁን ሕዝቦችን በሙሉ ተካፋይነት የሚጠይቅ ድርጊት እንደ መሆኑ ከዳር ለመድረስ ገና ሌሎች ተጋድሎዎች ፤ ሌሎች መሥዋዕትነቶች ይፈልጋል ። በየፈርጁ ጭቁን ሕዝቦች ለተሳትፎ ዝግጁ መሆን ፤ አብዮታቸውን ለማሳካት መብቃት ለአብዮቱ ዋና ዋስትናው ነው ። ለዚህ ደግሞ ጭቁን ሕዝቦች የተበታተነ ትግላቸውን አስተባብረው ፤ እጅ ለእጅ ተያይዘው አብዮቱን ለማራመድና ጠላቶቻቸውን ለመደምሰስ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው ተደጋግሞ ተገልጾአል ። በዚህም አንፃር የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከየካቲት ፲፱፻፷፮ ወዲህ የወሰዱት እርምጃ የማይናቅ ቢሆንም ወደፊት የሚቀረው ደግሞ ከዚህ የበለጠ አሳሳቢ ነው ። በንቃት በድርጅትና በትጥቅ የሚደረጉ ሌሎች ተጨማሪ እርምጃዎች አብዮቱ በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚፈጸም ያረጋግጣሉ ። የተደራጁና እጅግ የተዘጋጁ ጠላቶች ከዚህ በተለይ በምንም ዓይነት ሁኔታ እንደማይደመሰስ ደግሞ ግልጽ ነው ።

የኢትዮጵያ ሴቶችም ያው የነሱ ነፃነት ከጨቋኝና አድኃሪ ሥርዓት መገርሰስ በቀር በሌላ በምንም ተአምር ሊገኝ ስለማይችል በዚህ ፊውዳሊዝምን ፤ ኢምፔሪያሊዝምን ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን በሚደመስሰው አብዮት ውስጥ መካፈል ይኸ የካቲት ፳፱ የሚከበረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንም የኢትዮጵያ ሴቶች በዚህ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በመጨመር በዝባዥ ሥርዓትን ለመጣል ከሌሎች ጭቁኖች ጋር መሰለፋቸውን የሚያረጋግጡበት ነው ። ጭቁን ሴቶች የትም ይሁኑ የት ብዝበዛን ለመቋቋም የሚያደርጉትን ትግል ስለ



ሚያገናኛቸው የኢትዮጵያም ሴቶች የተጫነባቸውን ቀንበር ለመጣል የሚያደርጉት ትግል የሌሎች ትግሎች አካል ነው ። ስለዚህም ይኸ ቀን የኢትዮጵያ ሴቶች በፊውዳሊዝም ፤ በኢምፔሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ላይ ክንዳቸውን በማንሣት የሌሎች ታጋይ እኅቶቻችውን ትግል እንደሚያግዙ የሚያሳዩበት ቀን ነው ።

ኢምፔሪያሊዝም የዓለም ጭቁን ሕዝቦች በሙሉ ጠላት ነው ። በማንኛውም ሥፍራ የሚካሄድ አብዮት ኢምፔሪያሊዝም በጠላትነት የማያስቀምጥ ሊሆን አይችልም ። ስለዚህም በየትም ቦታ ያሉ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች በፀረ—ኢምፔሪያሊዝም ሊስት ይዞታቸው አንድነት አላቸው ። ማንኛውም ጭቆናን ለመጣል የሚደረግ ትግል የዓለም ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል አካል ነው ። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግልም ከዚህ ውጭ ሊሆን እንደማይችል ሁሉ የኢትዮጵያ ሴቶችም እንቅስቃሴ በፀረ—ኢምፔሪያሊዝም መድረክ ውስጥ የተሰለፈ ነው ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ሴቶች ይኸንን ቀን ሲያስቡት ከሌሎች ፀረ—ኢምፔሪያሊስት እንቅስቃሴዎች ጋር ያላቸውን የትግል አንድነት ይመሠርታሉ ። በፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ ሳሉ ሌሎች ሴቶች ድጋፋቸውንም ይሰጣሉ ። በዚህም የኢምፔሪያሊዝምን ከዓለም ግጽ መባረር ያፋጥናሉ ።

የኢትዮጵያ ሴቶች ይኸንን ቀን ሲያከብሩ በተለይ ባለፉት የትግል ዓመታት የተከናወኑ ድርጊቶችን በማስታወስ ካለፉት ስህተቶች ትምህርት በመቅሰም ለወደፊቱ ጉዞአቸው መንገዳቸውን ያስተካክሉ ። ያለፈውን ድካማቸውን ወደ ጥንካሬ ለውጠው ለመገስገስ የቀድሞ ድካማቸውን በጥንቃቄ ይመረምራሉ ። ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ከግቡ ለማድረስ በሚደረገው ትግል ውስጥ ሴቶች ተገቢ ቦታቸውን ይዘው ካልታገሉ የጭቁን ሕዝቦች የነፃነት ቀን የራቀ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም ። ስለዚህም በጠቅላላው የአብዮቱ ወዳጆች በንቃት በድርጅትና በትጥቅ ያሉዋቸውን ድክመች ለማስወገድ ሲሞክሩ ሴቶችም በተለይም ለየት ያሉ ድካሞቻቸውን ለማሸነፍ ይታገላሉ ። ለምሳሌም ንቃታቸው ከፍ እንዲል ፤ ጠላትና ወዳጆቻቸውን በትክክል እንዲለዩ ፤ ድርጅታቸው ተጠናክሮ የወዝአደሩ ፓርቲ ተመሥርቶ በዚያ ውስጥ ሴቶችም ታሪካዊ ቦታቸውን እንዲይዙ ፤ አብዮቱን ለመጠበቅ ለሚያስችላቸው ትጥቅም ይታገላሉ ።

የኢትዮጵያ ሴቶች ይኸንን ዓለም አቀፋዊ በዓል በብሔራዊ ደረጃ ሲያከብሩ ዘንድሮ ሁለተኛቸው ሊሆን ነው ። እስኪ መለስ ብለን ባለፈው ዓመት ይኸ ቀን የተከበረበትን ሁኔታ እንመልከት።

ባለፈው ዓመት የኢትዮጵያ ሴቶች በአጠቃላይ የነበራቸው ንቃት ከአሁኑ ሲወዳደር አነስተኛ ሆኖ ይታያል ። በገጠር እንኳን ከከተማው ሻል ያለ ንቃት አለ ለማለት ይቻላል ። ምክንያቱም አንደኛ የገጠር መሬት አዋጅ ያስከተለው ግልጽ የመደብ ትግል ሴቶችም በቀጥታ እንዲሳተፉ አድርጓቸዋል ። በትግል ውስጥ የሚገኝ ንቃት ደግሞ በሌላ ጊዜ በማንበብና በመወያየት ከሚገኝ ንቃት በተሻለ ፍጥነት በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ ለውጥን እንደሚያስከትል የታወቀ ነው ። ይኸም እንግዲህ የገጠር ሴቶችን ንቃት ከፍ ለማድረግ ረድቷል ማለት ነው ።

ሁለተኛ የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ምንም እንኳን ከአድኃሪውና ከአናርኪስቱ ከፍተኛ ተቃውሞ የተቀበለ ቢሆንም የአርሶ አደሩን ንቃትና ድርጅት ለማጠንከርና ለማሳደግ ያደረገው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው ። አድኃሪውና አናርኪስቱ ኢምፔሪያሊዝም ጭምር በተለያዩ ሰበቦች ሊያከሽፉት የታገሉትም አርሶ አደሩ ከነቃ ፤ ከተደራጀና ከታጠቀ የእነሱን የመጨረሻ ሞት የሚያቀርብ መሆኑን በደንብ ስለተረዱት ነው ። በገጠር ተሰማርተው የነበሩት ዘማቾች የመሬቱን አዋጅ ለማስፈጸም ከፍተኛ ተጋድሎ ከማድረጋቸውም በላይ የሴቶችን ማኅበራትም በመጠኑም ቢሆን አደራጅተዋል ። ይኸም የገጠር ሴቶችን ንቃትና ድርጅት ለማሳደግ የሰጠው ርዳታ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ነገር ግን ይኸም ሆኖ እንኳን የገጠር ሴቶች በአብዮቱ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ ሆነዋል ማለት አይቻልም ። ገና ረጅም የትግል ጉዞን የሚጠይቅ ሂደት ቀርቷል ። አዲሱን ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከግቡ ለማድረስ የሚያስችል ንቃትና ድርጅት አልተሟላም ። ገና የወዝአደሩ ፓርቲ ተመስርቶ በፓርቲው መሪነት ሌሎች ጭቁን ሕዝ

ቦች ተደራጅተው በፓርቲው መሪነት ሥራ የአንድነት ግንባር አልተመሠረተም ። ሴቶችም በአ ብዮታዊው ግንባር ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችል ብቃት አላገኙም ። ስለዚህም የገጠር ሴቶችም ገና ሊያሟሏቸው የሚገባ የንቃት ፣ የድርጅት ፣ የትጥቅ ደረጃ አለ ማለት ነው ። ባለፈው ዓመት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ሴቶች ያከበሩት ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሆንም ከንቃታቸው ዝቅተኝነት የተነሣ በድምቀት አላከበሩትም ። በዓሉ የነሱ መሆኑን እስከዚህም ስላልተረዱት በተለይ በገጠር ምንም ያህል አከባበር አልነበረውም ለማለት ይቻላል ።

በከተሞች ምንም እንኳን ጭቁን ሴቶች በደንብ ተሳትፈውበታል ባይባልም በመጠኑ ተከ ብሯል ። በየአካባቢው ያሉ የነቁ ሴቶች ይኸን በዓል ለማክበር እንደሚገባ በመቀስቀሳቸውና መን ግሥትም በዓሉ እንዲከበር በማድረጉ በዓሉ በሰልፎችና በስብሰባዎች እንዲታወስ ሆኗል ። ነገር ግን በከተሞች ውስጥ የተቋቋሙ የሴቶች ማኅበራት ይኸን ያህልም ነበሩ ለማለት አያስደፍርም ።

በተለይም በአዲስ አበባ ሴቶችን አደራጃለሁ የሚለው «የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ » የሴቶችን የመደራጀት ፍላጎት አፍኖ ይዞ እንደነበር ይታወሳል ። እንኳንስ በየክፍለ ሀገር ስላሉት ሴቶች ሊያስብና ለማደራጀት ጥረት ሊያደርግ ይቅርና በአዲስ አበባ እንኳን ሴቶችን ለማንቃትና ለማደራጀት ያደረገው ሙከራ አልታየም ። ከየቦታው ጥቂት በመያዝ እነሱንም አሁን ወደ ቅጥር ነፍስ ገዳይ ቡድን ለተለወጠው ኢ.ህ.አ.ፓ መጠቀሚያ መሣሪያ ለማድረግ ብቻ ሲፍጨረጨር ታይ ቷል ። በአለፈው ዓመት የካቲት ፳፱ የሴቶች ቀንም ቀደም ብሎ ዞር ብሎ አይቷቸው የማያ ውቀውን አንዳንድ ወዝአደርና ሌሎችም ሴቶች በዓል እንዲያደምቁለት ከሰበሰበ በኋላ ኰሚቴው የኢትዮጵያ ሴቶችን ወክሎ የመንግሥት ሥልጣን እንዲካፈል እንዲታገሉለት ጥሯል ። በዚያን ወቅት ከነበሩት መፈክሮች ውስጥ «የሴቶች ማኅበር በአስቸኳይ ይቋቋም» የሚለው በጣም ገናና እንደነበር ይታወሳል ። ይኸም የኢ.ህ.አፓ የእንስታይ ክንፍ የሆነው «የሴቶች አስተባባሪ ኰሚቴ» ራሱን ወደ ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር ለመለወጥ ለመንግሥት ሲያቀርብ የነበረውን አቤቱታ የብዙ ጭቁን ሴቶች ጥያቄ ለማስመሰል ያቀረበው ዘዴ ነበር ። አገር አቀፍ የሆነው የሴቶች ማኅበር የሚቋቋመው በተራማጆችና በጭቁን ሴቶች ረጅም ትግል ነው እንጂ መንግሥት በአዋጅ የሚመ ሠርተው እንዳልሆነ ግልጽ ነው ። ስለዚህም ያለፈው ዓመት ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በአዲስ አበባ ውስጥ ሲከበር አሁን ከመሳፍንቱ ጋር መቆሙ ተጋልጦ እርቃኑን የቀረው የኢ.ሀ.አ.ፓ ቡድን ሴቶች ጭቁን ሴቶችን በማወናበድ ለራሳቸው አላማና ለራሳቸው ጥቅም ያስለፉበት ቀን ነበር ለማ ለት ይቻላል ።

በአሁኑ ዓመት ግን በተራማጆች ፣ በቀራጥ ታጋዮች ተጋድሎና ጥረት ኢ.ሀ.አ.ፓ የወጣት መሳፍንትና የግልገል ፋሽስቶች ቡድን መሆኑ ተረጋግጦአል ። የወዝአደሩ ፓርቲ ነኝ እያለ በሰፊው ሕዝብ ላይ ሲያሾፍ እስከመቼም ሊዘልቅ አልቻለም ። ሴቶችም የዚህን ቡድን አድኃሪነት በመ ገንዘብ በየስልፉና በየስብሰባው ሲያወግዙት ይታያሉ ። የሴቶች አስተባባሪ ኰሚቴም ፈርሶ ጭቁን ሴቶች በራሳቸው ጥረትና በሀቀኛ ተራማጆች ርዳታ በመደራጀት ላይ ናቸው ። ስለዚህም ይኸ ዓመት ካለፈው በተሻለ ሁኔታ ጭቁን ሴቶች የራሳቸውን ጥያቄ የሚያነሱበት ፣ ለራሳቸው ጥቅም የሚታገሉበት እንጂ ለማንም አድኃሪና ለማንም ሥልጣን የጠማው ቀኝ ንዑስ ከበርቴ የሚስለፉ በት ቀን አይሆንም ። ካለፈው ስሕተታቸው ካለፈው ድካማቸው ተምረው አድኃሪ ኃይላትን ፊት ለፊትም መጡ የተራማጅ ካባ ለብሰው በማጋለጥና በመታገል ወደፊት ይጓዛሉ ። በትግላቸው የተቀዳጁትን ድል ጨብጠው ለሌሎች ከፍተኛ ድሎች ይገሰግሳሉ ። ስለዚህም ጭቁን ሴቶች የዘ ንድሮን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በታላቅ ድምቀት ያከብራሉ ። ከሌሎች ጭቁን ሴቶች ጋር የት ግል አንድነታቸውን ይጠብቃሉ ። ለነፃነታቸው ከሚታገሉ ሴቶች ጐን በመሰለፍ ኢምፔሪያሊዝ ምን ፣ ዘረኝነትን ፣ አፓርታይድን ይቃወማሉ ። ይታገሉታልም ።

የጭቁን ሴቶች ዓለም አቀፋዊ አንድነት ይለምልም ።